## እንግዶች እንኳን ደህና መጣችሁ!

## ማስታወቂያ

### የሕንጻ ፈንድ ማሰባሰብ ፕሮግራም

ለሕንጻ ግዢ ለመስጠት ቃል የገባነውን ገንዘብ በገባችሁት ቃል መሰረት የፈጸማችሁ ሁሉ እግዚአብሔር ይባርካችሁ። ለመስጠት ቃል የገባችሁ ደግሞ ስጦታውን እስከ አመቱ መጨረሻ (ወይንም ቃል በገባነው መሰረት) እንድንሰጥ እናበረታታችኋለን። የህንጻ ኮሚቴ አስተባባሪዎች።

### የአዲስ አመት ፕሮግራም

የችካጎና አካባቢው አብያተ ክርስቲያናት በብረሃነ ወንጌል ቤተ ክርስቲያን በአንድነት ማዕድ በመቁረስ፣ በጸሎት፣ በአምልኮ፣ ቃሉን በመካፈልና በልዩ ልዩ ፕሮግራሞች የአዲስ አመት ማዜማ ፕሮግራምን በጋራ ያካሂዳሉ። ሁላችንም በመገኘት የበረከቱ ተካፋዮች እንሁን።

### የልጅ በረከት

ወንድማችን ዶ/ር ታሪኩ እና እህታችን መዳኒት በወንድ ልጅ ተባርከዋል። እግዚአብሔርን ስለዚህ በርከት እናመስገናለን።

"ወደ ውጭም አውጥቶ፦ ጌቶች ሆይ፥ እድን ዘንድ ምን ማድረግ ይገባኛል? ኣላቸው።
እነርሱም፦ በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ እመን አንተና ቤተ ሰዎችህ ትድናላችሁ አሉት።" (ሐዋ. 16፥ 30-31)



⇒ የእሁድ ፕሮግራም ይካፈላሉ?
⇒ የአርብ ፕሮግራም ይካፈላሉ?
⇒ በምጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ይካፈላሉ?
⇒ ማገልገል ይፈልጋሉ?
⇒ Yeec.org App ጭነዋል?
⇒ http://www.yeec.org/ ይጎበኛሉ?


ሽማግሌዎችን ለማግኘት፦
773-886-0818 (ሲሳይ)
773-865-6102 (ብረሃኑ)
773-507-0194 (ጋሽ አያሌው)
773-910-0485 (ፒተር)
773-961-5332 (ጌቱ)


### መደበኛ ፕሮግራሞች

እሑድ 1:30 p.m. -- 4:30 p.m.
አርብ 7:00 p.m. -- 9:00 p.m.

# የችካጎ የምስራች ወንጌላዊት ቤተ ክርስቲያን

# Chicago Yemsrach Evangelical Church

"እነሆ፥ ለሕዝቡ ሁሉ የሚሆን ታላቅ ደስታ የምሥራች እነግራችኋለሁና አትፍሩ" ሉቃስ 2:10




## "ምስጋና የሚሠዋ ያከብረኛል..."

(መዝ. 50:23)


Chicago Yemsrach Evangelical Church
4455 N. Seeley Avenue
Chicago, IL 60625


### መደበኛ ፕሮግራሞች

እሑድ 1:30 p.m. -- 4:30 p.m.
አርብ 7:00 p.m. -- 9:00 p.m.

**December 10, 2017** | **ታኅሣስ 1፣ 2010 ዓ.ም.**

## የእለቱ አገልግሎት መርሃ-ግብር

| | |
|---|---|
| ጸሎት መሪ................ | እሕት ሰናይት ከበደ |
| አምልኮ...................... | የቤተክርስቲያን አምልኮ ቡድን |
| ፕሮግራም መሪ .......... | ወንድም ፒተር መኩሪያ |
| ቃል ........................... | ወንድም ብርሃኑ አንበሴ |
| ማጠቃለያ ................ | ፕሮግራም መሪ |

### <u>የሳምንቱ ጥቅስ</u>

"ሳታቋርጡ ጸልዩ፤ በሁሉ አመስግኑ፤ ይህ የእግዚአብሔር ፈቃድ በክርስቶስ ኢየሱስ ወደ እናንተ ነውና።"

(1 ተሰ. 5፡ 17-18)

**የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ቡድኖች**

| መሪ | ቀን | አድራሻ |
|---|---|---|
| ወ/ም አያሌው አስፋው | ማክሰኞ | 5030 N. Marine Dr., Chicago, IL 60640 |
| እህት ሰናይት ከበደ | ማክሰኞ | 7200 N. Ridge Ave., Chicago IL 60660 |
| ዶ/ር ተረፈ አንሼቦ | ማክሰኞ | 7526 N. Ridge Blvd., Unit #3W, Chicago IL 60645 |
| ወ/ም ረድኤቱ ካሳ | ሐሙስ | 7252 W. Everell Ave., Chicago, IL 60631 |
| ወ/ም ሳሚ ኃብተየስ | ሰኞ | 9107 Laramie St. Skokie, IL 60077 |
| ወ/ም ዮናስ ባህሩ | ማክሰኞ | 5523 N. Kenmore Ave., Chicago, IL 60640 |
| ወ/ም ሰለሞን ወመነ | ቅዳሜ | 549 Sheridan Rd., Apt. 3, Evanston, IL 60202 |
| ወ/ም መስፍን ጌታቸው | ዕሮብ | 4631 N. Beacon St., Chicago, IL 60640 |

## መልዕክተ ሰንበት

ወ/ም ረድኤቱ ካሳ

### <u>አመስጋኞች እንሁን</u>

*"ምስጋና የሚሠዋ ያከብረኛል፤ የእግዚአብሔርን ማዳን ለእርሱ የማሳይበት መንገድ ከዚያ አለ" ይለናል።" (መዝ. 50፡23)*

የምስጋና ከልብ የሚፈልቅ የአምልኮ መስዋዕት ነው። መጽሐፍ ቅዱስ ስለ ምስጋና ሲናገር "ምስጋና **<u>የሚሠዋ</u>** **<u>ያከብረኛል</u>**፤ የእግዚአብሔርን **<u>ማዳን</u>** ለእርሱ የማሳይበት መንገድ ከዚያ አለ" ይለናል። (መዝ. 50፡23) በዚህ ቃል የምናስተውለው አንዱ ነጥብ ምስጋና በእግዚአብሔር ፊት የሚቀርብ **<u>መስዋት</u>** እንደሆነ ነው። ምስጋና እግዚአብሔር በሕይወታችን ለሆኑት መልካም ነገሮች ማለትም ስላገኘናቸው በረከቶች፣ ስለ አስደናቂ ጥበቃው፣ በኛ ላይ ስለበዛው ምህረቱ እና ወደር ስሌለው ፍቅሩ እያሰብን ሁሉ የሆነልን ከርሱ የተነሳ እንደሆነና የመልካምነት ሁሉ ምንጭ እርሱ እንደሆነ ተገንዝበን ለርሱ ብቻ የምናቀርበው (ለሌላ የማናጋራው) መስዋዕት ነው። የእግዚአብሔርን አባትነት እያሰብን ምስጋና ስናቀርብ ምስጋናችን በእግዚአብሔር ፊት መልካም መዓዛ ያለው መስዋዕት ይሆናል።

ምስጋና አንዱ እግዚአብሔርን የምናከብርበት መንገድ ነው። ለዚህ ነው ቃሉ ምስጋና የሚሰዋ **<u>ያከብረኛል</u>** የሚለው። በምስጋና ወደ እግዚአብሔር ስንቀርብ በሕይወታችን እግዚአብሔር የሰራውን ስራ እውቅና መስጠታችን ነው። አንድ ጊዜ አስር ለምጻሞች "ኢየሱስ ሆይ ማረን" እያሉ እየጮሁ ወደ ጌታ መጡ። (ሉቃ. 17፡12) ጌታም አስሩንም ፈወሳቸው። ከነርሱም አንዱ እንደ ተፈወሰ ባየ ጊዜ "በታላቅ ድምፅ እግዚአብሔርን እያከበረ ተመለሰ።" (ቁ. 15) ጌታም "አሥሩ አልነጹምን? ዘጠኙስ ወዴት አሉ?" በማለት ጠየቀ። ከአንዱም በቀር እግዚአብሔርን ሊያከብር የተመለሰ አልነበረም። ብዙ ጊዜ ግን ከእግዚአብሔር ብዙ ነገር እንጠይቃለን፤ እርሱ ሲመልስልን ግን ለምስጋና አንገኝም። እንደ ዘጠኙ ለምጻሞች በረከታችንን ተቀብለን ለበረከቱ ጌታ ምስጋና ማምጣትን እንዘነጋለን። ለተደረገልን ነገር እግዚአብሔርን ማመስገን ይገባናል። ስናመሰግን እግዚአብሔርን እናከብራለን።

ምስጋና የእግዚአብሔርን **<u>ማዳን</u>** የምናይበት መንገድ ነው። እግዚአብሔርን የሚያመሰግን ሰው ከድል ወደ ድል፤ ከበረከት ወደ በረከት ይሸጋጋራል። ከላይ በተመለከትነው ክፍል ውስጥ ዘጠኙ የተፈወሱት ለምጻሞች በረከታቸውን ይዘው ሄዱ። ከተቀበለው በረከት ይልቅ በፈወሰው ጌታ የተደነቀው አንዱ ግን ለማመስገን ተመለሰ። በታላው ድምጽ (ሰው ሁሉ እየሰማ) እግዚአብሔርን አመሰገነ። ይህም ብቻ አይደለም ጌታን እያመሰገነ በጌታ እግር ላይ በግንባሩ ወደቀ። ጌታም "ተነሣና ሂድ፤ እምነትህ አድኖሃል አለው።" (ቁ. 19) ለዚህ ሰው የስጋ ፈውስ ብቻ ሳይሆን የነፍስ መዳን ሆነለት። በምስጋና የእግዚአብሔርን ማዳን አየ።

ወገኖቼ፡- ሁልጊዜ ስለሁሉ እግዚአብሔርን ልናመሰግን ይገባናል። ምስጋና በእግዚአብሔር ፊት የምናቀርበው መስዋዕት ነው። ምስጋና እግዚአብሔርን የምናከብርበት መንገድ ነው። ምስጋና የእግዚአብሔርን ማዳን የምናይበት ነው። አመስጋኞች እንሁን።